DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የበጋ መማሪያ (Summer Learning) የክሬዲት መልሶ-ማነሳሻ (Credit Recovery) መመሪያ/Guidance

*በስራ-ላይ የዋለው ጁን (June) 2024።*

ተማሪዎች - በኮርስ ክሬዲታቸው እንዲቀጥሉ እና በጊዜው-እንዲመረቁ ለመርዳት፤ የDCPS ተማሪዎች በበጋ (summer) ትምህርት ወቅት፣ በክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (Credit Recovery) ኮርሶች ውስጥ ተመዝግበው-መማር ይችላሉ። የDCPS የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (credit recovery) ፕሮግራም፣ ተማሪዎች በወደቁባቸው ኮርሶች - እንደገና መልሶ ማነሳሻን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረታቸው ላይ ድጋፍ-ለማድረግ የተቀረጸ-ነው። ክሬዲትን መልሶ ማነሳሻ (Credit Recovery) ኮርሶች፤ በየግል-ሁኔታ ላይ የተመረኮዘ/individualized እና በብቃት-ችሎታ ላይ መሠረት-ያደረገ ነው።

በበጋ መማሪያ (Summer Learning) የክሬዲት መልሶ-ማነሳሻ (Credit Recovery) ኮርሶች ውስጥ የሚካፈሉ - የDCPS ተማሪዎች፤ በመደበኛ የትምህርት-ዓመቱ ወቅት ውስጥ ኮርሶቹን እንደሚያገኙበት-አንድ ዓይነት በሆነ መንገድ፣ ከፍተኛ-ደረጃ ያለውን የቀለም-ትምህርት እርዳታዎች እና የትምህርት-አሰጣጥን ያገኛሉ። የክሬዲት መልሶ-ማነሳሻ ፖሊሲ (The *Credit Recovery Policy*)[1] ለክሬዲት መልሶ-ማነሳሻ ፕሮግራሙ፤ መገኘት-የሚችሉ ኮርሶች፣ለ ለኮርስ መልሶ-ማነሳሻ ብቁነትን፣ ለትምህርት-አሰጣጥ የሚፈቀዱ ፎርማቶች፣ የጊዜ-ሰሌዳ አወጣጥ እና የሠራተኛ-አመዳደብ፣ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance)፣ ኮርስን ማጠናቀቅ እና ውጤት-ደረጃ አሰጣጥ፣ የይግባኝ ሂደት እና የእንግሊዘኛ-ቋንቋን የሚማሩ እና ከጉዳተኝነት-ጋር የሚገኙ ተማሪዎችን ልዩ-በሆነ ሁኔታ ከግምት-ውስጥ ማስገባትን - ጨምሮ፤ የDCPS መስፈርቶችን ያስተላልፋል። የበጋ መማር (summer learning) ያለውን ባህሪይ-ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ አንዳንድ የፖሊሲ መስፈርቶች - መስተካከል ያለባቸው፣ እና የእነዚህም ለውጦች ዝርዝር ከዚህ-በታች ይገኛል። በዚህ ፖሊሲ ውስጥ - በተለየ-ሁኔታ ካልተጠቀሰ በስተቀር፣ ሌሎች *የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ ፖሊሲ (Credit Recovery Policy)* መስፈርቶች በሙሉ፣ የበጋ መማር የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ ፕሮግራሞች (summer learning credit recovery programs) ላይ ተፈጻሚ-ይሆናሉ።

## መገኘት-የሚችሉ ኮርሶች

በበጋ (summer) የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ወቅት፣ አካላዊ-ትምህርት (Physical Education) ሊገኝ-የሚችል የክሬዲት መልሶ-ማነሳሻ ሆኖ የሚሰጥ፣ እና ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ሊያቀርቡት ይችላሉ።

## የጊዜ-ሰሌዳ አወጣጥ እና የሠራተኛ-አመዳደብ (Scheduling and Staffing)

በበጋ (summer) መማር የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ ኮርሶች፣ እንደ የሠራተኛ-አመዳደብ ሞዴል አንዱ-ክፍል ሆኖ፤ የአስተማሪው-ከተማሪው ጋር ያለው መመጣጠን/ratio - 1-ለ-25 ከመሆን-መብለት የለበትም። አስተማሪዎች፣ ለሁለት (2) ኮርሶች ኃላፊነት-ሊወስዱ ይችላሉ፤ ነገር-ግን በሁለቱ (2) ኮርሶች መካከል የሚያገለግሏቸው አጠቃላይ-ቁጥር፣ ሃያ-አምስት (25) ተማሪዎች ብቻ ይሆናል።

## በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance)

በበጋ (summer) መማር የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ ኮርሶች ውስጥ፤ ተማሪዎች፣ በእያንዳንዱ-ሣምንት - በየቀኑ-በክፍሎቻቸው ውስጥ ተገኝተው-መማር-ይጠበቅባቸዋል (ማለትም፤ በመደበኛነት - በሣምንት ውስጥ አምስት (5) ቀናት)። የበጋ (summer) መማር ክፍለ-ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት - አስፈላጊ-የሆኑት ስራዎች (required materials)ን ተማሪው የሚያጠናቅቅበት - በብዛት-ያልተለመደ ሁኔታ በሚገጥም-ጊዜ፤ ይህ የሚጠበቅባቸው-ግዴታ (expectation) ሊስተካከል-ይችል ይሆናል። ይህ ውሳኔ፣ በአስተማሪያቸው የሚወሰድ እና፣ በተማሪው የትምህርታዊ መዝገብ ውስጥ በሰነድነት-መግባት አለበት።

በበጋ (summer) መማር ክፍለ-ጊዜው ውስጥ፣ ተማሪው ያለ-በቂ ምክንያት ለአራት (4) ቀናት ከቀረ፤ ከኮርሱ ይወጣሉ፣ እና በትምህርት-ውጤት ማረጋገጫቸው (transcript) ላይ እና/ወይም በሪፖርት ካርዳቸው ላይ፣ የ"W" ውጤት-ደረጃን ያገኛሉ። ከሁለተኛው፣ ሦስተኛው እና አራተኛው ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) በኋላ፣ የመቅረት ማሳወቂያዎች/Absence notifications - ለቤተሰቦች ይሰጣሉ። በበጋ (summer) መማር የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ ኮርስ - በትምህርት-ገበታ ላይ ባለመገኘት (attendance) ምክንያት “W” ያገኙ-ተማሪዎች፣ በዚያ በጋ (summer) ወቅት - ወደ ኮርሱ በድጋሚ-ገብቶ ለመማር ብቁነት አይኖራቸውም።

---

[1] *በ* https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies. *ላይ የሚገኝ*